# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

**ሕዳር 22 ቀን 2006 ዓ.ም.**

### የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ ተካሄደ

ከ ሕዳር 19 ቀን እስከ ሕዳር 21 2006 ዓ.ም. ባሉት ቀናት የተካሄደው 5ኛው የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በሀገራዊ በዓለም አቀፍና በድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ የሆነ ውይይት አድርጎና የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፎ ለሚመለከታቸው የፓርቲው አባላትና አካላት መመሪያዎችን አስተላልፏል ።

መደበኛው ስብሰባው ሀገራችን ያልችበትን ወቅታዊ ሁኔታ በጥልቀት መርምሮ ከተለያዩ ግንዛቤዎች ላይ የደረሰ ሲሆን ትግሉን ሊያጠናክሩ የሚችሉ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳልፏል። ቁንጮ በመሆን የወያኔን አምባገነነ ቡድን ሲያሽከረክር የቆየውን መለስ ዜናዊን የተካ ግለሰብ አለመከሰቱና በቡድኑ ውስጥ የውህደት ችግር መኖሩ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚቻል ቢሆንም አሁንም ቢሆን በስልጣን ላይ ያለው ይህ አጥፊ ቡድን በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው የሙብት ረገጣ አፈናና ብዝበዛ በሰፊው መቀጠሉን መደበኛ ስብሰባው ተገንዝቧል። የዜጎች ሙብት አለመከበሩን፤ የዜጎች አፈና እስራትና ግድያ በሰፊው የቀጠሉ መሆናቸውን፤በጋዜጠኞች፤ በመምህራን በተማሪዎች፤ በሰራተኞችና በአርሶ አደሮች ላይ እየተካሄዱ ያሉት አፈና፤ እስራትና ግድያ በሰፊው የቀጠሉበት ሁነታ መኖሩን፤ በሃይማኖቱ ውስጥ ጣልቃ የመግባትና የሃይማኖት ተቋሞችን በቡድኑ ቁጥጥር ስር የማድረጉ አስከፊ ተግባር በሰፊው ቀጥሎ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው የሙብት መገደብና አፈና ተጠናክሮ መቀጠሉን፤ በሳኡዲ አረቢያና በሌሎች ቦታዎች በደል ለሚደርስባቸው ወገኖቻችን ስቃይ ምንጩ የወያኔ አገዛዝ መሆኑን፤ ሕዝባችን በድህነት እየማቀቀና በዋጋ ግሽበት እየተሰቃየ የአገራችን አንጡራ ሀብት ግን አሁንም በገፍ እየተዘረፈ መሆኑን፤ ወያኔ የሀገራችንን መሬት ለባእዳን እየቸበቸበ አርሶ አደሩን ከመሬቱ እያፈናቀለና ችግር ላይ እየጣለ መሆኑና ሌሎችንም በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮችን በማንሳት መደበኛው ስብሰባ በሰፊው ተወያይቶ ከግንዛቤ ላይ ደርሷል። ወቅቱ የወያኔ አገዛዝ ከመቸውም ጊዜ በላይ ከሕዝብ የተነጠለበት በመሆኑ ሕዝባዊ ትግሉን አፋፋሞ ይህን አፋኝና አምባገነነ አገዛዝ ማስወገድ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ድምዳሜ ላይ ደርሷል።

መደበኛ ስብሰባው ከተለያዩ የፓርቲው ክፍሎችና ኮሚቴዎች የቀረቡልትን የስራ ዘገባዎች አዳምጦ ሰፋ ያለ ውይይት አካሄዷል። በአሁኑ ወቅት ፓርቲው በተለያዩ ዘርፎች እያካሄዳቸው ያሉት እንቅስቃሴዎች የሚያበረታቱና ተስፋ የሚሰጡ መሆናቸውን ተገንዝቦ በይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ወስኗል። ስብሰባው በሁለንተናዊ መንገድ የድርጅቱን ውስጣዊ ይዞታና ብቃት የሚያሟሉና አቅሙን የሚገነቡ እንዲሁም ትግሉን በይበልጥ ሊያጠናክሩ የሚችሉ ስልቶች ቀይሶ አስፈላጊውን የተግባር መመሪያዎች ለሚመለከታቸው የፓርቲው አባላት- አካላት አስተላልፏል።

መደበኛ ስብሰባው በተቃዋሚ ሃይል በኩል ያለውን እንቅስቅሴ አንስቶ በሰፊው የተወያየበት ሲሆን የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ የተባበረና የተቀናጀ ትግል ማካሄድ አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን በማስገንዘብ ፓርቲው በአገር ውስጥ በገቢር ተባብሮ ለመታገል በተደጋጋሚ ያደረገውን ጥሪ አሁንም አድሷል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217 fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ይህን በሕዝብ የተጠላውንና ከሕዝብ የተነጠለውን አምባገነኑን የወያኔን ቡድን ለአንዴም ለሁሌም አስወግዶ ሥልጣን በሕዝብ እጅ እንዲገባ ለማድረግ ኢሕአፓ  የጀመረውን ትግል በጽናት ለመቀጠል ቃል ኪዳኑን እያደሰ ሕዝባዊ ድጋፉና ትብብሩ እንዳይለየው ጥሪውን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላልፋል።

**በተባበረ ሕዝባዊ ትግል የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ይወገዳል!!**

**ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው!!**


EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel 202-291-4217    fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
website: WWW.EPRP.COM

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France